# ነገረ ጣና

(ሰንደቅ፤13ኛ ዓመት ቁጥር 635፣ ረቡዕ፣ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.)

• የጣና ሐይቅ በውስጡ ሃያ ሰባት ገዳማትን አቅፎ ይዟል፡፡

• በጣና ሀይቅና በዙሪያው የሚገኙት አብዛኞቹ ገዳማት ሰባቱ ከዋክብት በሚል መጠሪያ ከሚታወቁት የሃይማኖት አባቶች ጋር የተሳሰረ ታሪክ አላቸው፡፡

ጣና ሐይቅ ለኢትዮጵያ የታሪክና የማንነት መገለጫ የሆነ ግዙፍ ቅርስ ነው። ጣና ውስጥ እጅግ ድንቅ የሚባሉ የኢትዮጵያ ቅርሶች የሚገኙበት ምስጢራዊ ውኃ ነው። በርካታ እድሜ ጠገብ ጽላቶች፣ ንዋየ ቅዱሳት፣ ብርቅዬ የብራና መጻህፍት፣ የታላላቅ መሪዎችና ቅዱሳን አጽም፣ ከአሪት እስከ ሐዲስ ኪዳን የተንጣለለ ታሪክ፣ ብዙ ብዙ ገና ያልደረስንባቸው ምስጢራዊ ታሪኮች ያሉበት የኢትዮጵያዊያን ሁሉ መስታወት ነው። ይህ መስታወታችን እየደበዘዘ ሊሰባበር መንገዱን ይዞታል። እኛ ኢትዮጵያዊያን ይህን መስታወታችንን ከክፉ አደጋ የመጠበቅ ሀላፊነት አለብን። ጣና ከታመመ አባይም አዙሮ ይጥለዋል። ከጣና ማህጸን ስለሚወጣ ህመሙ ህመማቸው ነው።

ዓባይ ለኢትዮጵያ ትልቅ ታሪክ፣ የጥበበኞች ቋንቋ እና ሃይማኖት ሁሉ ሆኖ ቆይቷል። ለምሳሌ ዓባይ እየተንደረደረ ጥልቅ ብሎ የሚወጣበት ጣና ሃይቅ ከጎጃም እስከ ጎንደር ድረስ ተለጥጦ 3 ሺህ 600 ካሬ ኪሎ ሜትር ሸፍኗል። በዚህ ደሴት ላይ ከጥንታዊው ከአሪቱ ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ ይጸለያል፣ ይዘመራል፣ ይሸበሸባል። ምክንያቱም በሐይቁ ላይ 37 ደሴቶች አሉ። እነዚህ ደሴቶች ላይ ደግሞ ከ21 የሚበልጡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ገዳማት አሉ። ገዳማቱ ውስጥ የዓለም ታላላቅ ቅርሶችና ታሪኮች ያሉባቸው ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሣይንስ እና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/ ቱሪስቶች እንዲይዋቸው ደጋግሞ የሚወተውትላቸው አስገራሚ ቦታዎች ናቸው።

ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ የካቲት /መጋቢት 2001 ዓ.ም በሐመር መጽሔት ላይ ስለ ጣና ሐይቅ እንዲህ ብሏል፡- ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን ይህን ሐይቅ ጌታ በተወለደበት ወቅት በግብፅ ላይ ምርምር በማድረጉ የሚታወቀው ግሪካዊ ተመራማሪ ስትራቦ፣ "ሴቦ" በማለት ይጠራው ነበር። የሁለተኛው ክፍለ ዘመን የግብፅ መልክዓ ምድር ተመራማሪ የነበረው ገላውዴዎስ ፕቶሎሜም፤ "ኮሎ" ይለው ነበር። የአቴናው ድራማ ፀሐፊ ኤስኪለስ ደግሞ፣ "መደብ የተቀባይ ሐይቅ የኢትዮጵያ ጌጥ" ይለው ነበር። ይህ ሰው፣ ይህን ያለው ደግሞ አምስት መቶ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ መሆኑን ስናስብ በዚያ ዘመን፤ የዓለም ዓይኖች ከሚያርፍባቸው ሀገራት፣ ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም የነበረች መሆኗንም እንገነዘባለን።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሀይቆች ትልቁ የጣና ሃይቅ ነው። ስፋቱ 3 ሺህ 637 ካሬ ኪ.ሜ ሲሆን በውስጡ በሚገኙ ደሴቶችና በዙሪያው በርካታ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን የሚከተሉ ገዳማት ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ገዳማት ከ700 ዓመት እድሜ በላይ ያላቸውና ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተሰባሰቡ ውድ የታሪክ ቅርሶችና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታትን አጽም የያዙ ናቸው። በመሆኑም ገዳማቱ የአገሪቱ ቤተክህነት ሙዚየም ናቸው ለማለት ይቻላል።

## ደብረማርያም

ከባህር ዳር ከተማ የሰሜን ምስራቅ አቅጣጫን በመያዝ በጀልባ ለሃያ ደቂቃ አሊያም በእግር ለአንድ ሰዓት ተኩል በመጓዝና የአባይን ወንዝ በታንኳ በማቋረጥ የደብረ ማርያም ገዳም ወደምትገኝበት ደሴት መግባት ይቻላል። የተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶችን የያዘችው የደብረ ማርያም ገዳም በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት /1307-1337 ዓ.ም/ እንደተመሠረተች ይነገራል። አካባቢው በሁለት ተጨማሪ ስሞች ይታወቃል። እነኚህም ጉማሬ ባህር እና አባይ ራስ ይባላሉ። ጉማሬ ባህር የተባለው በአካባቢው ጉማሬዎች ስለሚገኙ ሲሆን አባይ ራስ የተባለው ደግሞ የአባይ ወንዝ የሀይቁን ውሃ ሰንጥቆ የሚወጣበት ስፍራ በመሆኑ ነው።

## ክብራን ገብርኤልና እንጦስ

ከባህር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የ45 ደቂቃ የጀልባ ጉዞ በኋላ ብዙም ያልተራራቁ መንትያ ደሴቶች ይገኛሉ። ደሴቶቹ የሚገኙት ማራኪ በሆነ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ባለውና በደን በተሸፈነ ኮረብታማ ስፍራ ነው። ደሴቶቹ ክብራን ገብርኤልና እንጦስ በመባል ይታወቃሉ። ክብራን ገብርኤል የወንድ፣ እንጦስ ደግሞ የሴት መናንያን መኖሪያ በመሆን ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት የእነጦስ መነኮሳት ወደ ሌላ አካባቢ መሰደዳቸው እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ገዳሙ ጠፍ /ባዶ/ ሆኖ መቆየቱ ይነገራል። አሁን ግን ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶና የኢየሱስ ታቦት ገብቶ ገዳሙ
ወደ ወንዶች ገዳምነት ተለውጧል።

የክብራን ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተሠራው በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ሲሆን በዳግማዊ ዳዊትና ኋላም በአዲያም ሰገድ ኢያሱ በድጋሚ እንደተሰራ ይነገራል። ቤተ ክርስቲያኑ በወጉ በተጠረቡ ቀያይ ድንጋዮች የታነፀ ነው። በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከድንጋይ የተጠረቡ 12 አምዶች ይገኛሉ። ከመቅደሱ ግድግዳ ጋር ተያይዞ በተሰራ ክፍል ውስጥ የገዳሙ መሥራች የአቡነ ዘዮሐንስ መቃብር ይገኛል። በደሴቱ አናት ላይ በታነፀው የክብራን ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም በአፄ ፋሲል እንደተሠራ በሚነገርለት ዕቃ ቤት ውስጥ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ በሐዋርያው ሉቃስ እንደተሣለች የሚነገርላት ሥዕለ ማርያም ከብረት የተሠራው የአቡነ ዘዮሐንስ የጸሎት ልብስ የአፄ ኢያሱ አልጋና ሰይፍ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተደራራቢ አልጋ ከእንጨት የተሠሩ መቅረዝና አገልግል መስቀሎቸ የገበታ ላይ ሥዕሎችና የብራና መጻሕፍት ይገኙባቸዋል። ወደ ክብራን ገብርኤል መግባት የሚፈቀድላቸው ወንዶች ናቸው።

## ዘጌ

ታላቁ የኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ሰው ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረየሱስ የተወለደባት ደሴት ነች። የጣናን ሀይቅ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በመገፋት ተንሰራፍቶ የሚታየው ባህረገብ መሬት /ፔኒንሲዩላ/ ዘጌ ይባላል። በቅርብ ርቀት ሆነው ሲመለከቱት ክንፉን ዘርግቶ የተቀመጠ አሞራ ይመስላል። ዘጌ ከባህር ዳር ከተማ 15 ኪ.ሜ ያህል የሚርቅ ሲሆን በጀልባም አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ያስኬዳል። በመኪና ደግሞ ሁለት ሰዓት ይፈጃል። ርቀቱም 23 ኪ.ሜ እንደሆነ ይገመታል።

በዘጌ ባህረ ገብ ምድር ላይ ሰባት የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። እነኚህም መሀል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ አቡነ በትረማርያም፣ አዝዋ ማርያም፣ ውራ ኪዳነ ምህረት፣ ደብረ ሥላሴ፣ ይጋንዳ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ፉሬ ማርያም ይባላሉ። ከመጨረሻዎቹ ሁለቱ በስተቀር ሌሎቹ ገዳማት አነስተኛ ጀልባዎችን ሊያስጠጉ የሚችሉ ወደቦቸ አሏቸው። በጣና ሀይቅና በዙሪያው የሚገኙት አብዛኞቹ ገዳማት ሰባቱ ከዋክብት በሚል መጠሪያ ከሚታወቁት የሃይማኖት አባቶች ጋር የተሳሰረ ታሪክ አላቸው። መነሻቸው ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሆነ የሚነገርላቸው እነኚህ ጻድቃን የሃይማኖት መሪዎች አቡነ ታዴዎስ፣ አቡነ ዘዮሐንስ፣ አቡነ በትረ ማርያም፣ አቡነ ኂሩት አምላክ፣ አቡነ አሳይ፣ አቡነ ዘካርያስና አቡነ ፍቁረ እግዚ ዮሐንስ ይባላሉ። አቡነ ታዴዎስ ደብረ ማርያምን፣ አቡነ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን፣ አቡነ በትረ ማርያም ፣ አቡነ ኂሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፣ አቡነ አሳይ ምንዳባን፣ አቡነ ዘካርያስ ደብረ ገሊላን፣ አቡነ ፍቁረ እግዚ ዮሐንስ ደግሞ ጣና ቂርቆስን እየገደሙ እንዳቀኑ ይነገራል። ከዘጌ ገዳማት በእድሜ አንጋፋ እንደሆነ የሚነገርለት የመሃል ዘጌ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያኑ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተመሠረተ የመሥራቹን የአቡነ በትረ ማርያምን ገድል ዋቢ በመጥቀስ ካህናቱ ይገልጻሉ። አቡነ በትረ ማርያም ከሸዋ ልዩ ስሙ ሙገር ከተባለ አካባቢ እንደመጡ ይታመናል። በመሀል ዘጌ ጊዮርጊስ በርካታ ጥንታዊ ቅርሶች ይገኛሉ። ከብረት የተሠራው የአቡነ በትረ ማርያም የጸሎት ልብስ የጥንት ነገሥታትና መኳንንት ስጦታዎች የብራና መጻሕፍት ከቅርሶቹ ጥቂቶቹ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኑ በተለያየ ጊዜ የመፍረስና እንደገና የመሠራት ዕድል ቢገጥመውም የጥንቱን እደ ጥበብ የሚመሰክሩ የእንጨት ቅርጻ ቅርጾች በመስኮቶቹና በሮቹ ላይ አሁንም አሸብርቆ ይታያል። ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ጥንታዊ ገጽታቸውን ጠብቀው ከቆዩት ጥቂት ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ የሆነው የበትረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ይህ ቤተ ክርስቲያን አቡነ በትረ ማርያም ካረፉ በኋላ ረዳታቸው በነበሩት በአቡነ በርተሎሜዎስ አማካኝነት በመቃብራቸው ላይ ለመታሰቢያነት

የተተከለ ነው። ውስጡ ባማሩ ጥንታዊ የሃይማኖት ሥዕሎች ያሸበረቀውና በከብ ቅርጽ ተሰርቶ በባህላዊ የሳር ክፍክፍ የተከደነው የበትረ ማርያም ቤተክርስቲያን የጥንቱን ዘመን የቅርጻ ቅርጽ ጥበብ የሚዘክሩ በሮችና መስኮቶች አሉት። በጥንታዊ ቅብ ሥዕሎች ከሚታወቁት የዘጌ ገዳማት አዝዋ ማርያምና ውራ ኪዳነ ምህረት ሳይጠቀሱ የሚታለፉ አይደሉም። በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደተሠራች የሚነገርላት አዝዋ ማርያም በመቅደስዋ ዙሪያ ያማሩ የግድግዳ ቅብ ሥዕሎችን የያዘች ነች። አንዳንዳቹ ሥዕሎች ዙሪያቸው በብር ጉባጉብቶች የተዋቡ ናቸው። በዘጌ የሚገኙ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሥዕሎች የተሰሩት በአዝዋ ማርያም ስለነበር አንዳንድ ጊዜ ሥዕል ቤት ተብላ ትጠራለች። የውራ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በአቡነ ዘዮሐንስ እንደተመሠረተች ይነገራል፡ ፡ አቡኑ ከሸዋ መርሃቤቴ የመጡ ሲሆን በቀድሞው ደብረ አስባ ገዳም በአቡነ ሕዝቅያስ እጅ ቅስና እንደተቀበሉ በጣና ሃይቅ ደቡባዊ ምስራቅ ዳርቻ በደራ ወረዳ ከሚኖሩ ጥቂት የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ጋር ቆይታ አድርገው ወደ ክብራን ደሴት እንደሄዱ ገድላቸው ያትታል። ውራ ኪዳነ ምህረት በክብ ቅርጽ የተሠራች ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ናት። የቅኔ ማህሌቱ ከሸንበቆ ቅድስቱና መቅደሱ ከጭቃና ከድንጋይ የተሠሩ ሲሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ጣሪያው በሳር ክፍክፍ የተሸፈነ ነበር። የመቅደሱ ዙሪያ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተሣሉ የሚነገርላቸው ውብ የሃይማኖት ሥዕሎች ያጌጠ ነው። ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት፣ የነገሥታት ዘውዶች ካባዎችና መስቀሎች ከታሪካዊ ቅርሶቿ ናቸው። ውራ ኪዳነ ምሕረትን ወንዶችም ሴቶችም ሊጐበኟት ይችላሉ። በዘጌ ባህረገብ መሬት ላይ የጣና ሀይቅንና አካባቢውን ሰፊ በሆነ አድማሳዊ ርቀት ለመመልከት የሚያስችል የአራራት ተራራ አለ። በዚህ ተራራ አናት ላይ የይጋንዳ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። አፄ አዲያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት እንደተመሠረተ የሚነገርለት ይህ ቤተ ክርስቲያን በቅርስ ከምችታቸው ከሚታወቁት የዘጌ ገዳማት አንዱ ነው። ከሀይቁ ዳር ወደ ይጋንዳ የሚወስደው የእግር መንገድ አቀበት የበዛበት ሲሆን ቢያንስ አንድ ሰዓት ያስኬዳል።

## ደቅ ደሴት

ጣና ሀይቅ ካሉት ደሴቶች ትልቁ ደቅ ደሴት ነው። ከባህር ዳር ከተማ ሰሜናዊ አቅጣጫ 37 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ይህ ደሴት የሰባት ደብር አገር ተብሎ ይታወቃል፤ ምክንያቱም ከደሴቱ በቅርብ ርቀት የሚገኘውን ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ጨምሮ ሰባት አድባራትን ስለያዘ ነው። እነዚህም ናርጋ ሥላሴ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ኮታ ማርያም፣ ዝባድ ኢየሱስ፣ ጆጋ ዮሐንስና ጋደና ጊዮርጊስ ናቸው። ደቅ የሚለው ቃል በግዕዝ ልጅ ወይንም ትንሽ ማለት ሲሆን ደሴቱ ከሌሎች ደሴቶች ትልቁ ሆኖ ሳለ ለምን ይህ ስም እንደተሰጠው በውል አይታወቅም። ደቅ ደሴት መጀመሪያ ለመነኮሳት ብቻ እንጂ ለዓለማውያን ኗሪዎች ያልተፈቀደ ነበር። ኋላ ግን ቀስ በቀስ በርካታ ሰዎች ወደ ደሴቱ በመምጣት በመስፈርና በመዋለድ የኗሪው ቁጥር ከፍ ሊል ችሏል። የደሴቱ ኗሪዎች አማርኛ ተናጋሪና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ናቸው። የአካባቢው ኗሪዎች ወደ ደሴቱ ሕዝብ በብዛት የገባበትን ዘመን በአራት የተለያዩ ጊዜያት ከፋፍለው ይናገራሉ። የመጀመሪያው በግራኝ አህመድ ጦርነት፣ ሁለተኛው እቴጌ ምንትዋብ የናርጋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንን በሚያሠሩበት ወቅት፣ ሦስተኛው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት፣ አራተኛው ደግሞ በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመነ መንግሥት በነበረው የድርቡሾች ወረራ ወቅት ነበር። ደቅ ደሴትን ከሌሎች ደሴቶች ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የቀድሞ ነገሥታት የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውንና ተቃዋሚዎቻቸውን በግዞት የሚያቆዩበት ቦታ በመሆኑ ነው የሚሉ የታሪክ ጸሐፊዎች አሉ። ለምሳሌ በአፄ ሕዝብ ናኝ ዘመን የደብረ ጽሞና ገዳም መሥራች በነበሩት በአባ ሲኖዳ ላይ ንጉሡን የሚቃወም ንግርት ተናግረናል በሚል ክስ ቀርቦባቸው በአፄው ትዕዛዝ ወደ ደቅ ደሴት እንደተጋዙና ሕይወታቸውም እዚያው እንዳለፈ በዲማ ጊዮርጊስ የሚገኘው ገድላቸው ያትታል። በክረምት ወራት በሃይቁ ሙላት ሳቢያ ወደ ደሴትነት የሚለወጠውና በበጋው ወራት ውሃው ሳይጎድል የደቅ ምዕራባዊ አካል በመሆን ደሴቱን የሚቀላቀለው የናርጋ ሥላሴ ገዳም የወንዶችና የሴቶች የቁሪት ገዳም በመባል ይጠራል። ገዳሙን ያሠሩት የአፄ በካፋ ባለቤት የነበሩት እቴጌ ምንትዋብ /1730-1755/ ናቸው። የናርጋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብ ቅርጽ ከድንጋይ ከኖራና ከእንጨት የተሠራ ሲሆን ቁመታቸው አራት ሜትር ስፋታቸው ደግሞ ሁለት ሜትር የሆኑ ስምንት ግዙፍ በሮች አሉት። መቅደሱ በጥንታዊ የሃይማኖት ሥዕሎች ያሸበረቀ ነው። ሥዕሎቹ የተሣሉት በመቅደሱ ዙሪያ ሲሆን በስተምዕራብ

የክርስቶስን ታሪክ ከልደት እስከ ዕርገት፣ በስተደቡብ የቅድስት ማርያምን ስደትና ተአምራት፣ በስተምስራቅ የክርስቶስን ተአምራት፣ በስተሰሜን ደግሞ የሰማዕታትን ገድል ይዘክራሉ። ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ የተሠሩ የጎንደር ዘመን የኪነ ህንጻ ጥበብ የሚንፀባረቅባቸው ባለፎቅ የጥበቃ ማማዎችና የሌሎች ሕንጻዎች ፍርስራሾች በግቢው ውስጥ ይገኛሉ። የእቴጌ ምንትዋብና የልጃቸው የአፄ ኢያሱ አልጋዎችና ካባ ልዩ ልዩ የብራና መጻሕፍትና የእጅ መስቀሎች በቅርስነት ተቀምጠዋል።

በደቅ ደሴ ምዕራባዊ አቅጣጫ ዙሪያዋን በትላልቅ ዛፍ ተከባ የምትገኝ ጥንታዊ ገዳም አለች። ቆላ ቅድስት አርሴማ ትባላለች። በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት እንደተመሠረተች ይነገራል። በአሁኑ ሰዓት ከአንድ ጠንካራ ገበሬ ቤት ብዙም ልቃ የማትታየው የቅድስት አርሴማ ገዳም ታቦቷ አባ ዮሐንስ በተባሉ መነኩሴ ከኢየሩሳሌም እንደመጣ የገደሚ ካህናት ይገልጻሉ። በስሟ ቤተ ክርስቲያን የቆመላት ቅድስት አርሴማ ከደናግልት ጋር ወደ አርመንያ ተሰዳ ለዕምነቷ ብዙ ፈተናን የተቀበለች በኋላም የተሰየፈች ሰማዕት እንደነበረች ገድሏ ላይ እንደተጻፈ ይነገራል። ከመቅደሱ አናት ላይ በአብዛኛው ደብዝዘው የሚታዩት የግድግዳ ቅብ ሥዕሎች የሰማዕቷን ገድሎች ይተርካሉ። በደቅ ደሴት ላይ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች የሚነገርላት ኮታ ማርያም ናት። ቤተ ክርስቲያኗ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በነበሩት በአባ ኂሩተ አምላክ እንደተመሠረተች የገዳሟ ካህናት ይገልጻሉ። ኮታ ማርያም በክብ ቅርጽ የታነፀች ዙሪያዋ ከእንጨት ከጭቃና ከኖራ የተሰራ ጣሪያዋ በሳር ክፍክፍ የተከደነ ነው። ወለሉ ደግሞ በጥንቃቄ ተሰንጥቀው በጠፍና በተያያዙ ሸንበቆዎች ተሸፍኗል። ጣሪያውን ደግፈው የያዙት 12 ረዣዥምና ወፋፍራም አምዶች ናቸው። በመቅደሱ ዙሪያ የተገጠሙት መስኮቶች ልዩ የቅርጻ ቅርጽ ጥበብ ይታይባቸዋል። በ1978፣ በ1983 አና በ1984 ዓ.ም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኗ አካሎች በባህል ሚኒስቴር የቅርስ ጥገና ባለሙያዎች የተወሰነ እድሳት ተደርጎላቸዋል። በመቅደሱ ግድግዳ ላይ የነበሩት ጥንታዊ የቅዱሳን ሥዕሎች ግን ከእድሜ ብዛትና ከእንክብካቤ ጉድለት ክፉኛ ተጐድተዋል። ከጣና ሃይቅ ደሴቶች ለደቅ ደሴት የሚቀርበው የዳጋ ደሴት ነው። ደሴቱ ከሃይቁ ከፍ ብሎ የሚገኝ በመሆኑ ከማንኛውም የሃይቁ ዳርቻ ሊታይ ይችላል። ዳጋ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነና በውስጡ የእስጢፋኖስን ገዳም የያዘ ነው። እንደ ገዳሙ ካህናት አስተያየት የዳጋ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት በአቡነ ኂሩተ አምላክ እንደተመሠረተ ይታመናል።

የዳጋ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በቅርፁ ከሌሎቹ የሀይቁ ገዳማት የተለየ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ በመርከብ ቅርጽ የተሰራ ሲሆን ምሳሌውም በጥፋት ውሃ ዘመን የሰው ዘር በኖህ መርከብ አማካይነት መዳኑን ለማመልከት እንደሆነ መነኮሶቱ ይናገራሉ። ዳጋ እስጢፋኖስ በርካታ መናኒያን መነኮሳት የሚገኙበትና ትክክለኛው የገዳም ሕይወት ሥርዓት የሚታይበት ሥፍራ ነው። ገዳሙን ልዩ ከሚያደርጉት ባህሪያት በመካከለኛው ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት አፅፅምት ሳይፈራርሱ በክብር ተቀምጠው መገኘታቸው ነው። ነገሥታቱ በሕይወት ዘመናቸው ለገዳሙ ያበረከቷቸው ስጦታዎችም በገዳሙ እቃ ቤት በቅርስነት ተቀምጠው ይገኛሉ። ዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ ነው።

*አቅራቢ ዮናስ ግደይ አገዘ*